# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 292 ታህሳስ 4 2006 ገጽ 1

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሁለገብ የትግል ስትራቴጂን በአማራጭነት ሲወስድ ከወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን የደቡብ አፍሪቃ አፓርታይድ ሥርዓትን ለመለወጥ የነበረውን ፍቱንነት በጥልቀት በማጤን ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔዉ ጋጠወጥ ፍርድ ቤት የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን ባልፈጸሙት ወንጀል ተከላከሉ ብሎ በየነ

የሰብዓዊ መብታቸዉ አንዱ አካል የሆነዉ የማምለክ መብታቸዉ እንዲከበር በመጠየቃቸዉ ብቻ በወያኔ የጸጥታ ኃይሎች ታድነዉ ከአንድ አመት በላይ በግፍ ታስረዉ የቆዩት የድምጻችን ይሰማ መሪዎች ዜጎችን ለማጥቃት ሆን ተብሎ የተፈጠረዉ የወያኔ ፍርድ ቤት ተከላከሉ ብሎ እንደበየነባቸዉ ጠበቃ ተማም አባ ቡልጉ ተናገሩ። የየስሙላ ፍርድ ቤቱ አስር ሁለት እስረኞችን በነጻ የለቀቀ ሲሆን እነ አቶ አቡበከር አህመድና ሌሎች ደግሞ የተመሰረተባቸዉን ሽብር አነሳስታችኋል የሚል ክስ እንዲካለከሉ ብይን ሰጥቷል። አንደ ተከሳሾቹ ጠበቃ እንደ አቶ ተማም አባ ቡልጎ አባባል ሙራድ ሹኩር ጀማል፣ ኑሩ ቱርኪ ኑሩ፣ ሼህ ባህሩ ኡመር ሸኩር እና ጋዜጠኛ የሱፍ ጌታቸው ሽብርን በመርዳት በሚለው ህግ አንቀጽ ሰባት ተጠቅሶባቸዉ ክሱን ተከላከሉ የተባሉ ሲሆን ተከሳሾች መከላከያቸውን ከጥር 22 እስከ 27 እንዲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል።

ውሳኔውን በተመለከተ አስተያየታቸውን ለኢሳት ቴሌቪዥንና ሬድዮ ቃለ መጠይቅ የሰጡት የተከሳሾቹ ጠበቃ አቶ ተማም አባ ቡሉጎ፣ ምንም እንኳ ተከላከሉ የተባሉት አንቀጽ የቅጣት መጠኑን ቢቀንሰውም፣ የእሳቸዉ አላማና ፍላጎት ግለሰቦቹ በነጻ ተለቅቀዉ ወደ ቤተሰቦቻቸዉ እንዲመለሱ ማድረግ ነዉ ብለዋል። የወያኔ አገዛዝ የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን መጀመሪያ ላይ የከሰሳቸዉ የሽብር ጥቃት ፈጽማችኋላ በሚል ጠንከር ያለ ክስ ቢሆንም ይህንን መሰረተ ቢስ ክስ የሚደግፍ መረጃ እንዳልተገኘ ጠበቃ ተማም አባ ቡልጎ ተናግረዋል። ብይኑ ሲሰጥ በእስረኞች ቆጠሩ ንጽበኩል ምንም አይነት የመደናገጥ ወይም የመረበሽ ምልክት አለማየታቸውን የተናገሩት ጠበቃው፣ የእኛ ደንበኞች ለምን እንደታሰሩ የሚያውቁ የሀይማኖት መምህራን እና ለእኛ ጽናትን የሚያስተምሩ ናቸው ብለዋል ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ሰመጉ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ዉስጥ ወያኔ የዜጎችን ሰብአዊ መብት መርገጡን አጋለጠ

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዉስጥ ባካሄደው ጥናት ባለፈዉ አመት ከክልሉ አማራ ናችሁ ተብለዉ በተባረሩ በብዙ ሺዎች በሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎች ላይ የክልሉ ባለስልጣኖችና የወያኔ የጸጥታ ኃይሎች የሰብአዊ መብት ጥሰት እና አካላዊ ጉዳት ማድረሳቸዉን አረጋገጠ። በክልኩ በተለያዩ ዞንና ወረዳዎች ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ቁጥራቸው ከ10 ሺህ በላይ የሚገመቱ ዜጐች ለረዥም አመታት ይኖሩበት ከነበረው አካባቢያቸው የዚህ ክልል “ተወላጆች አይደላችሁም” በማለት በሀይልና በግዳጅ ቤት ንብረታቸውን ጥለው ከመጋቢት 15/2005 ዓ.ም ጀምሮ እንዲሰደዱ መደረጋቸውን ተቋሙ አውስቷል፡፡

የሰመጉ የጥናት ቡድን በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ቡለን እየተባለ በሚጠራዉ ወረዳ ባካሄደዉ ጥናት ህፃናትና ሴቶች እንዲሁም አቅመ ደካማዎች በቂ ምግብና ህክምና ባለማግኘታቸው በከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀው እንደነበር አረጋግጦ የጉዳዩን ስፋትና ተፈናቃዩች በአሁኑ ግዜ የሚገኙበትን አጠቃላይ ሁኔታ ለማጣራት መቻሉንም ገልጿል።ተፈናቃዮቹ አሁን የሚገኙበት ሁኔታ አስቸጋሪ ነው ያለው የጥናቱ ሪፖርቱ፤ በአንዳድ አካባቢዎች ለምሳሌ በካማሼ ዞን ተፈናቃዮቹ ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ የተደረገ ቢሆንም ከተመለሱ በኃላ ንብረታቸው በመወሰዱና በመጥፋቱ ለመቋቋምና ወደ ነበሩበት የኑሮ ሁኔታ ለመመለስ አልቻሉም ። በተለይ ተፈናቃዮቹ ለእርሻ ግብዓት የሚሆኑ እንደ ዘር ፣ማዳበሪያ የመሳሰሉትን ለመግዛት ወይም ብድርም ለመውሰድ በሞከሩባቸዉ አማራ በመሆናቸዉ ብቻ አድሎ እንደተደረገባቸዉ ለማወቅ ተችሏል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የሶማሌ ክልል የወያኔ ጦር መኮንኖች ገንዘብና ንብረት እንዲያካብቱ የሚላኩበት ቦታ መሆኑ ተሰማ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ባለዉለታዎቼ ናቸዉ የሚላቸዉን ትግርኛ ተናጋሪ የሆኑ ወታደራዊ መኮንኖች ወደ ሶማሌ ክልል በመላክ ከፍተኛ ህብትና ንብረት አጋብሰዎ እንዲመለሱ ሆን ብሎ መንገድ አንደሚያመቻችላቸዉ አዲስ አበባና ጅጅጋ ዉስጥ የሚገኙ ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸዉ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ሀለጹ። በሙሰኝንት የተጨማለቀዉ የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ የመከላከያ አዛዦቹ ሶማሊ ክልል ዉስጥ እንዲመደቡ በማድረግ ከክልሉ መንግስት ጋር በመተባበር ከፍተኛ ሀብት አጋብሰው በቋሚነት ወደሚኖሩበት ቦታ እንደሚመልሳቸዉ ለማወቅ ተችሏል።ነበአሁኑ ጊዜ ተቀማጭነታቸው ጅጅጋ የሆኑት እና በክልሉ ቁጥር አንድ ሀብታም የሚባሉት /ወ/ት ሀዋ የሌተናንት ጄኔራል ዮሀንስ ገ/መስቀል ሁለተኛ ሚስትና የልጅ እናት ሲሆኑ፣ ግለሰቧ ከተራ ጫት ነጋዴነት በአንድ ጊዜ በብዙ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ሀብት ለማጋበስ የቻሉት በፍቅር ጓደናቸው አማካኝነት መሆኑን ጉዳዩን በቅርብ የሚያውቁ ሰራተኞች ለኢሳት ገልጸዋል።

ጄኔራል ዮሐንስ ከወ/ት ሀዋ ጋር የተዋወቁት በኮሎኔልነት ማእረግ የምእራብ ጎዴ አዛዥ በነበሩበት ወቅት ሲሆን፣ በወቅቱ ክልሉ ያወጣውን የምእራብ ጎዴን የካናል ጠረጋ የመከላከያ ሰራዊት እንዲያሸንፍ በማስደረግና የሰራዊቱ አዛዥም ስራውን ወ/ት ሀዋ ኩባንያ አቋቁመው በሰብ ኮንትራትነት እንዲሰጣቸው በማድረግ በአንድ ጊዜ ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ትርፍ እንዲያገኙ አድርገዋቸዋል። በጄኔራል ዮሀንስና በወ/ት ሀዋ መካከል ያለው የፍቅር ግንኙነት እየደራ ሲሄድ፣ ወ/ት ሀዋ ከፍተኛ ሀይል እየተሰማቸው ከታክስ ጋር በተያያዘ ጥያቄ የሚያቀርቡባቸውን የክልል ሰራተኞችን ሳይቀር የመከላከያን መኪኖች ይዞ በመሄድ በማስፈራራት ከግብር ራሳቸውን ነጻ ሲያደርጉ መቆየታቸውን ምንጮች ይናገራሉ። ወ/ት ሀዋ ከፍቅር ጓደኛቸው ከጄ/ል ዮሐንስ ጋር በመሆን ባቋቋሙት ኩባንያ በጅጅጋ ሁለት ታላላቅ ፎቆችን የገነቡ ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ ያለምንም ጫረታ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ሀብት የፈሰሰባቸውን ፕሮጀክቶች እንዲሰሩ ተፈቅዶላቸዋል። ( ወደ ገጽ 3 ዞሯል )

## ኢትዮጵያ ዉስጥ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦትን አሁንም በከፍተኛ ችግር ዉስጥ መሆኑ ተነገረ

ባንድ በኩል ለፓርቲ ካምፓኒዎች ሙሉና ያልተቋረጠ ግልጋሎት፣ በሌላ በኩል ጋም ጋም ላለ ፖለቲካ ማብረጃነት እያገለገለ ያለው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ችግሮች ከዚህ በፊት በሃይል እጥረት ምክንያት ይባል ስለነበር ፋሽስት ወያኔ ሃይል ገነባሁ በማለት የትየለሌ ሪፖርት በማቅረቡ አቅርቦቱና አገልግሎቱ ይሻሻላል ተብሎ ሲጠበቅ እንደነበር አይዘነጋም። ሆኖም ግን በመዲናዋ አዲስ አበባ ጨምሮ በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ከፍተኛ ሃይል እጦት ለሰአታት ሳይሆን ለቀናት አንዳንዴም ለሳምንታት የቀጠለ መሆኑ እየተዘገበ ይገኛል፡፡

ምንም እንኳ ፋሽስት ወያኔ ይህንን የሃይል ችግር የሃይል ተሸካሚ ገመዶች ማርጀት እያለ ምክንያት ከመደርደር የተቆጠበ ባይሆንም፤ ከወገኖቻችን የተነጠቀ ሃይል ለጅቡቲ እየተበረከተ መሆኑንም ስናስታውስ በወያኔ አተያይ እኛ ባለቤቶቹ በሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ ላይ እንደምንታይ ያሳያል የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም።

ሰሞኑንም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች በማለት ሪፖርተራችን እንደጠቆመው ከሆነ የፋሽስት ወያኔው ተላላኪ ሃይለማሪያም ደሳለኝ በአባይ ግድብ ግንባታ ሰበብ ከግብጽ ጋር ትሰለፍብኛለች ብሎ የጠረጠራትን ሱዳንን ለማረጋጋት ከወገኖቻችን የተነጠቀና ወገኖቻችንን በጨለማ ውስጥ የጣለ ኤሌክትሪክ ሃይል ለሱዳን ለማበርከት ላይ ታች ሲል እንደነበር ምንጮች ጠቁመዋል። ስለሆነም ምንም እንኳ የወያኔ ቁንጮዎች ይህን ወይም ያን እያሉ እያስተባበሉ ቢሆንም የገጠጠው እውነት ግን ለወያኔ የቢዝነስ ኢምፓየር እና ለፒለቲካ ማብረጃነት የሚውል የኤሌክትሪክ ሃይል እንዳልታጣ የሚያሳይ ሲሆን፤ ፋሽስት ወያኔ ቁጥሩ የበዛ የኤሌክትሪክ ሃይል ግንባታ ሪፖርት ቢያሰማም ሰፊው ሕዝባችን ግን ሽ ቢታለብ እንኳ ያው በገሌ ነው እያለ በጨለማ ውስጥ መቀመጡን ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ ዘግባል።

## ግንቦት 7 የቀድሞውን የነጻነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላን ሞት በማስመልከት መግለጫ አወጣ

“በአፓርታይድ የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ብቻ ሳይሆን በዩ. ኤስ. አሜሪካ ጭምር ሽብርተኛ ተብለው ሲሳደዱ፣ ሲታሰሩና ሲሰቃዩ የሕይወታቸውን አጋማሽ የጨረሱ፤ በሠላማዊ የታገዘ አመጽንና ሕዝባዊ እምቢተኝነትን አጣምሮ የያዘ ሁለ-ገብ ትግል በመምራት ለአፓርታይድ አገዛዝ ማብቃት ከፍተኛ ድርሻ ያለው የትግል አስተዋጽዖ ያደረጉ፤ ለመላው ዓለም የነፃነት ታጋዮች አርአያ የሆኑ” በማለት ኔልሰን ማንዴላን የገለጸው የግንቦት 7 መግለጫ “ኔልሰን ማንዴላ ታላቅ የነፃነት አርበኛ፣ ታላቅ የለውጥ አራማጅ፣ ታላቅ መምህር እና ታላቅ የእርቅ ሰው ነበሩ። ዓለም እኚህን ታላቅ አፍሪቃዊ አጣች። ካለ በኋላ “ኔልሰን ማንዴላ በሕይወት ቢለዩንም በመንፈስ አብረውን ይቆያሉ” ሲል መልካም ስራቸውም ከዓለም ሕዝብ ጋር አብሮ እንደሚኖር በማስረገጥ ጠቁሟል ግንቦት 7 በመግለጫው።

## ሁለገብ-ገብ ትግል - ከኔልሰን ማንዴላ ጋር የምንጋራው የትግል ስትራቴጂ

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄም በኔልሰን ማንዴላ ዜና እረፍት የተሰማውን ሐዘን በመግለጽ መግለጫ ያወጣ ቢሆንም የትግል ተሞክሯቸው ለአገራችን ስላለው ጠቀሜታ ተጨማሪ ቁም ነገሮችን ማንሳት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።

ኔልሰን ማንዴላንና የትግል ጓዶቻቸው መሣሪያ እስከማንሳት ያደረሳቸው የደቡብ አፍሪቃ አፓርታይድ አገዛዝ ዋነኛው መገለጫው የባንቱስታን ሕግ ነበር። በዚህ ህግ መሠረት ደቡብ አፍሪቃ ዘርን መሠረት ያደረጉ አስር "ባንቱስታ" የተሰኙ "ራስ ገዝ" ግዛቶች ተቋቁመው ነበር። ያኔ በደቡብ አፍሪቃ አገዛዝ ሥር በነበሩ የደቡብ ምዕራብ ግዛቶች ደግሞ ሌላ አስር ባንቱስታዎች ነበሯቸው። በእያንዳንዱ ደቡብ አፍሪቃዊ መታወቂያ ባንቱስታው እንዲገልጽ ህጉ ያስገድዳል። የአንዱ ባንቱስታ ነዋሪ ያለልዩ ፈቃድ ወደሌላው ባንቱስታ መሄድ አይችልም። ከዚህም ሌላ ለነጮች ብቻ በተከለሉ ቦታዎች ጥቁሮች ለሥራ ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ማናቸው ተግባር እንዳይገኙ ህጉ ያዛል። አፓርታይድ የደቡብ አፍሪቃ ዜጎችን በየዘር ክልሎቻው ውስጥ አጉሮ አገራቸውን እስር ቤታቸው እንዲሆን አደረገው። ይህንን ለመቃወም ኔልሰን ማንዴላ እና የወቅቱ ታጋዮች በመጀመሪያ ሰላማዊ ትግልን ሞከሩ፤ ያ አላዋጣ ሲል መሣሪያ አነሱ።

በአሁኑ ሰዓት ባንቱስታን መሰል የክልል አስተዳደር ያለው በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ነው። ልክ በአፓርታይድ ደቡብ አፍሪቃ እንደነበረው ሁሉ የኛም መታወቂያዎች ዘራችንና ክልላችንን ይገልፃል። በአፓርታይድ ደቡብ አፍሪቃ እንደነበረው ሁሉ እኛም ከክልላችን ውጭ ተንቀሳቅሰን መሥራትና መኖር አንችልም። ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ እና ከደቡብ ክልሎች ተፈናቅለው ለጎዳና ኑሮ የተዳረጉት የአማራ አርሶ አደሮች የዚህ ፓሊሲ ሰለባዎች ናቸው።

ኔልሰን ማንዴላ እና ድርጅቱ ኤ. ኤን. ሲ. በሰላማዊ ትግል ብቻ አፓርታይድን ማስወገድ እንደማይቻል የተገነዘቡት ከስዊቶ እልቂት ነው። በስዊቶ እልቂት 176 ዜጎች እንደተገደሉ ይነገራል። እኛ አገር ብዙ ስዌቶዎች አሉ። በበደኖ፣ በአዋሳ፣ በሀረር፣ በጋምቤላ፣ በጎንደር፣ በኦጋዴን፣ በአዲስ አበባ እና በሶማሊያ የደረሱት እልቂቶች እያንዳንዳቸው የስዌቶን እልቂት ያክላሉ። በዚህም ላይ በሰቲትና በሁመራ የተደረገው ስልታዊ የዘር ማጥራት፤ የወጣቶች ያላባራ ስደት የዚሁ ፓሊሲ አስከፊ ውጤቶች ናቸው።

ሰላማዊ ትግል ብቻውን የደቡብ አፍሪቃ ዘረኛ አገዛዝን ማስወገድ አልቻለም። ሰላማዊ ትግል ብቻውን ወያኔ በአገራችን ላይ የጫነብን ዘረኛ አገዛዝ እንዲያበቃ ማድረግ ይችላል ብሎ ማመን አዳጋች ነው። ስለዚህም ነው ማንዴላ እንዳደረገው ሁሉ ግንቦት 7 ም ሁለገብ ትግልን እንደ ትግል ስትራቴጂ ለመያዝ የተገደደው።

ሁለገብ ትግል ሕዝባዊ አመጽ እና ሕዝባዊ እምቢተኝነትን አጣምሮ መያዝ ይጠይቃል። ሁለገብ ትግል መጨከንን ያም ሆኖ ለእርቅ አንድነት ለሀገር እና ለወገን የጋራ ጥቅም መሥራትን ይጠይቃል። ሁለገብ ትግል ዘረኝነትን በጽናት የመታገል ሆኖም ግን ይቅር ባይ መሆንን ይጠይቃል።

ግንቦት7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሁለገብ የትግል ስትራቴጂን በአማራጭነት ሲወስድ ከወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን የደቡብ አፍሪቃ አፓርታይድ ሥርዓትን ለመለወጥ የነበረውን ፍቱንነት በጥልቀት በማጤን ነው።

ዘላለማዊ እረፍት ለኔልሰን ማንዴላ

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## የወያኔ 40 በ 60 እና 10 በ 90 የቤት ስራ ዕቅድ ገንዝብ መዝረፊያ መንገድ መሆኑ ተረጋገጠ

የወያኔ አገዛዝ 40 በ 60 እና 10 በ 90 ብሎ የጀመረዉ የቤት ልማት ዕቅዱ በድምሩ ከአንድ ሚሊዮን በላይ አገር ዉስጥና ዉጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንን መዝግቦ ገንዘባቸዉን ከተቀበለ በኋላ ቃል የገባዉን ልማት ለማካሄድ አለመቻሉን ከአገር ቤት የሚደርሱን ዜናዎች ጠቆሙ። በውጭ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የገንዘብ አቅሙ ላላቸው የአገር ዉስጥ ዜጎች የ40 በ60 አዲስ አበባ በአነስተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ ዜጎች ደግሞ የ10 በዘጠናና የ20 በ80 የቤት ስራ ጅምሮችን ያቀፈዉ የወያኔ የቤት ልማት ዕቅድ በችግር ላይ ችግር እያጋጠመዉ ምንም ያክል ወደ ፊት መራመድ አለመቻሉ በስፋት እየተነገረ ነዉ። በዚህ የቤት ልማት ዕቅድ አገር ዉስጥ በ10/90 850 ሺ በ 20/80 ደግሞ 350 ሺ የአዲስ አበባ ነዋሪ ተመዝግቦ እድሉን በመጠባበቅ ላይ ሲሆን ከ12 ሺ በላይ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያም በ40 በ60 በሚባለው ውስጥ ታቅፈዉ እድላቸዉን እየተጠባበቁ ቢሆንም በመርሀግብሩ ዝግጅት የተሳተፉ የውስጥ ምንጮች እንደገለጹት የወያኔ አገዛዝ ይህን እቅድ ለማሳካት ከፍተኛ የሆነ ፈተና ገጥሞታል ።

በባዶ ሜዳ ላይ ዕቅድ ማዉጣት የለመደዉ የወያኔ አገዛዝ የቤት ልማት እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ 2 ሚሊዮን የሚደርሱ ቤቶች መገንባት የሚኖርበት ሲሆን ይህን ያክል ብዛት ያለዉ ቤት ለመገንባት ደግሞ ቢያንስ 30 ሺ ሄክታር ስፋት ያለው ቦታ ያስፈልጋል። ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸዉ ወገኖች አስረግጠዉ እንደሚናገሩት ደግሞ አዲስ አበባ ዉስጥ ይህንን ያክል ሰፊ መሬት ማግኘት በፍጹም አይቻልም። የማዕከላዊዉ መንግስት ለአዲስ አበባ ከተማ ሰፋ ያለ የማስተር ፕላን በማዘጋጀት በማስተር ፕላኑ ውስጥ የኦሮሚያ ልዩ ዞኖች የሚባሉትን ሱሉልታን፣ ሰንዳፋንና ገላንን በማካተት በቂ የቤት መስሪያ ቦታዎችን ለማፈላለግ እቅድ ነድፎ እየተንቀሳሰ ቢሆንም ፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ግን " ከእንግዲህ መሬት ለአዲስ አበባ መስተዳድር መሬት የምንሰጠው በመቃብራችን ላይ ነው" የሚል አቋም ወስዶ በአቋሙ እንደጸና ነዉ።

በኦሮሚያ ክልል አቋም አጣብቂኝ ውስጥ የገባው የፌደራሉ መንግስት ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ባለስልጣናትን በመሰብሰብ እና አንድ ኮሚቴ በማዋቀር ወደ ክልሎች ልኳቸዋል። እነዚህ ባለስልጣኖች ወደ ተለያዩ ክልሎች በመሄድ አዲስ አበባ ዉስጥ ቤት እንዲሰራላቸዉ ገንዝብ ለከፈሉ የዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን በየክልሉ የቤት መስሪያ ቦታ እያፈላለጉ ነዉ። ክልሎች ቦታ ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆኑ ደግሞ የወያኔ ሁለተኛዉ ስራ እንደለመደዉ ወደ ዳያስፖራ በመምጣት ቤት ለማሰራት ገንዘባቸዉን የሰጡትን የዲያስፖራዉን አባላት ከአዲስ አበባ ወጣ ብለው በክልሎች ግንባታ እንዲያካሂዱ ማግባባት ሊሆን እንደሚችል ዉስጥ አዋቂ ምንጮች በእርግጠኝነት በመናገር ላይ ናቸዉ።

መንግስትን የገጠመው ሌላው ፈተና የገንዘብ እጥረት ነው። ንግድ ባንክ ለቤቶች ግንባታ የሚሆን 12 ቢሊዮን ብር ብድር መስጠት የሚኖርበት ሲሆን፣ በቅርቡ የንግድ ባንኩ ፕሬዚዳንት ከጠ/ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ ጋር በተገናኙበት ወቅት ባንካቸው ማበደር የሚችለው 6 ቢሊዮን ብር ብቻ መሆኑን ገልጸውላቸዋል። አቶ ሀይለማርያምም ባንኩ ቢያንስ 10 ቢሊዮን ብር ማበደር እንዳለበት ትእዛዝ ሰጥተዋል። ባንኩም ለታዋቂዎቹ የመጠጥ አምራች ድርጅቶች ማለትም ለሀይነከንና ዲያጎ የቢራ አምራች ፋብሪካዎች ፈቅዶት የነበረውን የ3 ቢሊዮን ብር የብድር ውል በመሰረዝ፣ ድርጅቶቹ 560 ሚሊዮን ብር ብቻ እንዲበደሩ በማድረግ ቀሪውን ገንዘብ ለዚሁ ፕሮጀክት ለማዋል ተስማምቷል። ባንኩ እስካሁን 8 ቢሊዮን ብር ለማሰባሰብ የቻለ ሲሆን፣ የመንግስትን ጥያቄ ለማሙዋላት ተጨማሪ 2 ቢሊዮን ብር ከየት እንደሚያመጣ ግልጽ አልሆነም።

በሌላ በኩል ደግሞ የቤቶች መስሪያ ዋጋ መጀመሪያ ከታቀደበት መጠን እንዲከለስ ተደርጓል። በመጀመሪያ ለ3 መኝታ ቤት መስሪያ የተመደበው ገንዘብ 385 ሺ የነበረ ሲሆን በተከለሰው አዲስ ዋጋ ግን ይህ ዋጋ በእጥፍ አድጎ 779 ሺ ብር እንዲሆን ተደርጓል። ይህ ዋጋ በቅርቡ እየታየ ያለውን የዋጋ ንረት ግምት ውስጥ በማስገባት ወደ አንድ ሚሊዮን እንደሚጠጋ ምንጮች ገልጸዋል። ዲያስፖራው ይህን ገንዘብ ግማሹን በአንድ ጊዜ ቀሪውን ደግሞ በአንድ ወር ውስጥ እንዲከፍል ይጠበቅበታል። አስገራሚው ነገር ይላሉ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች፣ መንግስት ከሚሰራው ቤት የተሻለ ጥራት ያለው ቤት በ450 ሺ ብር ማግኘት መቻሉ ነው።

ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም ሌላው ችግር የሆነው ተናቦ ለመስራት አለመቻል መሆኑን የውስጥ አዋቂዎች ይገልጻሉ። ለቤቶች ግንባታ ሃላፊነት በተሰጣቸው ሚኒስትር መኩሪያ ሀይሌ፣ በአዲስ አበባው ከንቲና ድሪባ ኩማ፣ በንግድ ባንክ ፕሬዚዳንትና በውጭ ግንኙነት ሚ/ሩ ቴዎድሮስ አዳህኖም መካከል መናበብ በመጥፋቱ ፕሮጀክቱ ባለበት የቆመ ሲሆን፣ በተለይም እያንዳንዱ ባለስልጣን ኢህአዴግን ከመውደቅ ያዳንኩት እኔ ነኝ ለማለት ሁሉም የራሱን እቅድ አውጥቶ ሳይናበብ እየሰራ መሆኑን ምንጮች ተናግረዋል።

## የወያኔዉ ጋጠወጥ ፍርድ ቤት የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የወያኔዉ የይስሙል ፍርድ ቤት የተመሰረተባቸውን ክስ ተከላከሉ የበየነዉ አቡበከር አህመድ፣ አህመዲን ጀበል መሃመድ፣ ያሲን ኑሩ ኢሳአሊ፣ ከሚል ሸምሱ ሲራጅ፣ በድሩ ሁሴን ኑር ሁሴን፣ ሼህ መከተ ሙሄ መኮንን፣ ሳቢር ይርጉ ማንደፍሮ፤ መሃመድ አባተ ተሰማ፣ አህመድ ሙስጠፋ ሃቢብ፣ አቡበከር አለሙ ሙሄ፣ ሙኒር ሁሴን ሃሰን ፣ ሼህ ስኢድ አሊ ጁሃር፣ ሙባረክ አደም ጌቱ አሊዬ እና ካሊድ ኢብራሂም ባልቻን ሲሆን በነጻ ያሰናበተዉ ደግሞ ሃሰን አሊ ሹራብ፣ ሼህ ሱልጣን ሃጂ አማን፣ ሼህ ጀማል ያሲን ራጁኡ፣ ሼህ ጣሂር አብዱልቃድር፣ ሃሰን አቢ ሰኢድ፣ አሊ መኪ በድሩ፣ ሼህ ሃጂ ኢብራሂም ቱሃሬ፣ ሼህ አብዱራህማን ኡስማን ከሊል፣ ወይዘሮ ሃቢባ መሃመድንና ዶክተር ከማል ሃጂ ገለቱን ነዉ።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

## ነጋሪቱም ተጎስሟል፤ፋኖም ተሠማርቷል !!!

ዛሬ ኢትዮጵያዊያን እያዩ ያሉት ውርደት ቃል የሚገልፀው አልሆነም። ኢትዮጵያ በታሪኳ ዛሬ እየደረሰ ያለ ዓይነት ውርደት ደርሶባት እንደሆነ በታሪክ የተመዘገበ ነገርም ተፈልጎ አልተገኘም። ይሄ ለኢትዮጵያዊያን የጨለማ ዘመን ነው። በኢትዮጵያ እንዲህ ስደትና እንግልት፤ ሃዘንና ዋይታ የበዛበት ዘመን ታይቶ አይታወቅም።

በዚህ ግዜ በኢትዮጵያችን መንግስት ነኝ እያለ ራሱን የሚጠራ ቡድን አለ።ይሄ ቡድን አገሪቷን ከተቆጣጠረ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ የገባችበት የውርደት አዘቅት ከባድ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በህወሃቶች አዝማችነት ተስምቶ የማይታወቅ ጆሮን ጭው የሚያደርግ ግፍ በዜጎች ላይ ይፈፀማል። የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ይዘው ግብረ ሶዶም እንዲፈፀምባቸው ያደርጋሉ፤ ሴቶች ልጆችን በጋራ ሁነው ይደፍራሉ፤ በተቀደሱ ስፍራዎች ገብተው ቅዱሱን ስፍራ ያረክሳሉ፤ ዜጎችን ከእርሻ ማሳቸው አፈናቅለው በገዛ አገራቸው መፃተኛ ያደርጓቸዋል። በአጠቃላይ ዜጎች በአገራቸው ተስፋ አጥተው ሃዘንተኛ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። ተስፋ የቆረጡ ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ ከምኖር ሂጄ ብሞት ይሻለኛል ብለው እግራቸው በመራቸው መንገድ ይሰደዳሉ። በእንዲህ ሁኔታ ከኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ250ሺህ በላይ ወጣቶች ይሰደዳሉ።ገሚሱ በየበርሃው በውሃ ጥማት ወድቆ ይቀራል፤ ገሚሱም የባህር አዞ ቀለብ ሁኖ ዱካው ይጠፋል። ከሞት ተርፈው በየአርብ አገራቱ የደረሱ ዜጎች በሰው ልጆች ላይ ሊደርስ የማይገባ ወንጀል ይፈፀምባቸዋል።ባንዲራቸውን በአንገታቸው እንደጠመጠሙ ሬሳቸው ሜዳ ላይ ተጥሎ የአርብ መሳቂያ መሳለቂያ ይሆናሉ። በዚህ ሰሞን በሳውዲ ዓረቢያ እየተፈፀመ ያለው ግፍ ለኢትዮጵያዊያን ትልቅ ብሄራዊ ውርደት ሁኗል።

ይሄ በእንዲህ እንዳለ "መንግስት ነኝ " እያለ ራሱን የሚጠራው ህወሃት በዜጎቹ ሲቃና መከራ እየቀለደ ይገኛል።አንድ ግዜ ዜጎቼን እያወጣሁ ነው ይላል፤ ሌላ ግዜ ደግሞ የሥራ ፈቃድ የሌላቸው ስለሆኑ አላውቃቸውም ይላል። ህወሃቶች በዚህ ብቻ አላበቁም በኢትዮጵያዊያኑ ላይ እየተፈፀመ ያለውን ግፍ ለማስቆም አዲስ አበባ በሚገኘው በሳውዲ እምባሲ ፊት ለፊት ሠላማዊ ሠልፍ እንዳይደረግ መከልከል ብቻ ሳይሆን ለሠላማዊ ሰልፍ የወጡ ዜጎችን የቻሉትን ያክል ወደ እስር ቤት አግዘዋል፤ ያገኙትን ሁሉ በቆመጥ እንዲደበደቡ አድርገዋል። የአካል ጉዳትም አድርሰዋል። ይሄን ሁሉ ግፍ የሚታደግ፤የህዝቡንም ሮሮ የሚሳማ መንግስታዊ አካል አልተገኘም። ዓለምም ፊቷን ያዞረችብን የሚመስል ሁኔታ ታይቷል።

ኢትዮጵያዊያን ቀና ብለን በኩራት በአርብ አገራት ጎዳናዎች ላይ የምንመላለስ ዜግች ነበርን። ስማችን ያማረ፤ ማንነታችን የተከበርን ዜጎች ነበርን። አረብ የሚያከብረን እንጂ እንዲህ የሚንቀንና የሚያዋርደን ዜጎች አልነበርንም። በዘመነ ህወሃት ግን ያ ሁሉ ክብራችን ተዋርዶ ዜጎቻችን እንደ ሌጦና ቆዳ በገንዘብ የሚሸጡ ሆኑ። በኢትዮጵያችን ላይ የነበሩ የቀድሞው ገዥዎች ምንም እንኳ ጨቋኞች ቢሆኑም ዜጎቻቸው በሌላ በማንም እጅ እንዲገላቱና እንዲዋረዱ የሚፈቅዱ አልነበሩም።በአንድ ወቅት አፄ ኃ/ ስላሴን" ሠራተኛ ይላኩልኝ" ብለው የሳውዲው ንጉስ ሲጠይቋቸው "ለመሆኑ ምንድ ነው የምትፈልጉት መሃንዲስ ነው ወይስ ሃኪም "ብለው ይጠይቋቸዋል። አይ "እኛ የምንፈልገው በቤት ሠራተኛነት የሚያገለግሉንን ነው" ይላሉ አረቦቹ።አይ "እኛ ለቤት ሠራተኛ የሚሆን ዜጋ የለንም" ብለው መለስውላቸዋል።ለራሱም ሆነ ለወገኑ ክብር ያለው መሪ መልሱ እንዲህ እንጂ ሳውዲ ድረስ ሂዶ ዜጎቹን ለባርነት ለመሸጥ ሲዋዋል አይገኝም።

ደሳለኝ ኃ/ማሪያም ከስድስት ወር በፊት ሳውዲ ድረስ ገስግሶ ሂዶ የቤት ሠራተኞችን ለአረቦቹ ለመላክ ተዋውሎ መመለሱ የሚታወስ ነው። ይሄን ውል ሲዋዋል ግን ስለ ክፍያ፤ ስለ ዕረፍት ግዜ፤ በህመም ግዜ ምን ይሆናል የሚሉ መሠረታዊ ቁም ነገሮች በውሉ ውስጥ አልተካተቱም። በእነዚህ ነገሮች ምክንያት የኢንዶኔዥያ እና የፊሊፒንስ መንግስታት ግን ምንም እንኳ ድሃ ብንሆንም ዜጎቻችንን የምንሰደው የታወቀ የክፍያ መጠን፤ የእረፍት ግዜ፤ የህመም ፈቃድ እነዚህንና ሌሎችን መሠረዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ የተሟላ የህግ ድንጋጌ ሲኖራችሁ ነው። ይህን ህግ እስከምታበጁ ዜጎቻችን የእናንተ መጫወቻ እንዲሆኑ አንልክም ብለው እምቢ ማለታቸው ይታወቃል። ህወሃት መራሹ መንግስት ግን ስለውጪ አገር አኗኗር ምንም ዓይነት ግንዛቤ የሌላቸውን ወጣት ልጆችን ያለ ምንም ህግ ከለላ አሳልፎ ለባእዳን ይሰጣል። ወጣት ሴቶችንና ወንዶችን ለግርድናና ለአሽከርነት የመላኩ የድለላ ሥራም ህወሃቶች ባቋቋማቸው ድርጅቶች ተካሂዶ ከዚህ ንግድ በተገኘው ገንዘብ ህውሃቶች ብዙ ገንዘብ አፈሱ። ወገኖቻችን ግን በአረቦች እጅ እንባቸውን በመዳፋቸው የሚሰፍሩ ሆነው ቀሩ።

ለዚህ ሁሉ መከራ እና ውርደት ያበቃን ምንድ ነው የሚል ርዕስም የሰሞኑ የመወያያ ርዕስ ሆኗል። የመከራውና የውርደቱ ምንጭ ፈርጀ ብዙ ቢሆንም ህወሃት ዋነኛው የችግሩ ምንጭ ስለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። በአጠቃላይ ግን ህወሃት መንግስት ነኝ ብሎ ሲያበቃ ዜጎችን ለመታደግ ምንም ዓይነት ተግባራዊ እንቅስቃሴ አለማድረጉ ብቻ ሳይሆን ዜጎች በሰላማዊ ሰልፍ እንኳ ቁጣቸውን እንዳይገልጹ መከልከሉ ማንነቱን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው።ለዚህ ብሄራዊ ውርደትና መከራ በመጀመሪያ ደረጃ ሊጠየቅ የሚገባው ህወሃት እንጂ ሌላ ማንም አይደለም። ህወሃት የኢትዮጵያዊያን ጠላት መሆንን የመረጠ የጠባብ ዘረኞች ቡድን ነው። ዜጎቻቸን እንዲህ ላለው ጉስቁልናና ውርደት እንዲጋለጡ ያደረጋቸው ህወሃት መሆኑን መያዝ ለነፃነት ለሚደረገው ትግል አንዱ አካል ነው።

የተከበራችሁ ወገኖቻችን፤

በሳውዲ አረቢያ የሚሰቃዩ ዜጎችን በተመለከተ ህወሃቶች ምንም ተቆርቋሪነት ያሳዩበት ሁኔታ እንዳልታየ ታውቃላችሁ።ለወገን ተቆርቋሪነት ከህወሃቶች የሚጠበቅ ስላልሆነ እኛ አንደነቅም። አስቀድመው በገንዘብ አሳልፈው ለሸጧቸው ዜጎች ይቆረቆራሉ ብሎ መጠበቅ የህወሃቶችን ባህሪይ ካለመረዳት የሚመነጭ ብቻ ሳይሆን ህወሃቶች ዜጎች ማኩረፊያ አገር እንኳን እንዳይኖሯቸው የሚያሴሩትን ሴራ ለመረዳት ካለመፈለግ የሚመነጭም ጭምር ነው። ወደ አረብ አገር የተሰደዱም ሆኑ በሌሎች አገር በስደት ላይ ያሉ ዜጎች በከፋቸው ግዜ ተመልሰው የሚገቡበት ሥፍራ አላቸው ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ በኢትዮጵያ የለም። ጉራፈርዳ እና ቤንሻንጉል አገርህ አይደለም ተብሎ የተባረረ ወጣት መግቢያው የት ነው ? ከዚህ ሥፍራ ወደ ሳውዲ የተሰደደ ወጣት መመለሻው ወደየት ነው? በዚያች አገር ድንጋይ ለመፍለጥ እንኳ የኢሕአዴግ አባል እንዲሆን በሚገደድበት አገር ምን አገር አለኝ ብሎ ነው የከፋው ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሰው? አዎን ኢትዮጵያዊያን ማኩረፊያ አገር የሌለን ከርታታ ዜጎች እንድንሆን ተደርገናል።አገር ያሳጡንም ህወሃቶች ናቸው እንጂ ሌላ ማንም አይደለም።

እንግዲህ ምን ይደረግ?

ይሄ ጥያቄ ግልጽና ቀላል መልስ አለው።አምርሮ መነሳት። ህወሃቶች በአዲስ አበባ ላይ ወንድ ልጅን አስገድደው ግብረ ሶዶም እንዲፈፀምበት ሲያደርጉ ሰምቶ "እነዚህ ምን ዓይነት አረመኔዎች ናቸው" ማለት ብቻ በቂ አይደለም።ለአረመኔ የሚገባውን ቅጣት ለመስጠት የአያቶቻችንን ጋሻና ጦር ማንሳት ግዜው የሚጠይቀው ታሪካዊ ግዴታ ነው። በሳውዲ አረቢያ በወገኖቻችን ላይ እየተፈፀመ የቆየውን ውርደት እንምባ ብቻ የሚያስቆመው አይሆንም። እንዲህ የአረብ መቀለጃ የሆነውን ማንነታችንና ክብራችንን አስመልሰን አንገታችንን ቀና አድርገን በአርብ ጎዳናዎች ላይ እንደቀድሞው ዘመን በኩራት እንድንመላለስ የአያቶቻችንን ትጥቅ ከተሰቀለበት አውርደን መታጠቅ ግዴታችን ሁኗል።

ግንቦት ሰባት ንቅናቄ ውስጥ ያለን ኢትዮጵያዊያን በወገኖቻችን ላይ እየተፈፀመ ያለው ውርደት ብሄራዊ ውርደት ነው እንላለን። ከዚህ በላይ ሌላ ብሄራዊ ውርደት የለም። ለዚህ ውርደት ያደረሰንም ህውሃት ነው። ህወሃት እስካለ ድረስ ብሄራዊ ውርደታችን ይቀጥላል እንጂ አይሻሻልም። እኛ የሚደርስብንን ውርደት ለማስቆም አምርረን ተነስተናል። እኛ እንዲህ ተዋርደን መኖርን ከቅድሞዎቹ ኩሩዎች አያቶቻችን አልተማርንም።እኛን ባንዳዎችና የባንዳ ልጆች ህወሃቶች አንገታችንን አስደፍተው አዋርደው አይገዙንም። አያቶቻችን ለነፃነታቸው እና ለአገራቸው ክብር ሲሉ በቆሙበት በጀግኖች ሥፍራ ለመቆም መንገዱን ጀምረናል። ከእንግዲህ ወዲያ ከዚህ ጉዞ የሚያቆመን ምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል የለም። ለእኛ ነጋሪት ከተጎሰመ ቆይቷል እኛ የነጋሪቱን ድምፅ በሰማን ግዜ ሳናቅማማ ተነስተናል።

እናንተስ ሳትቅማሙ ለመነሳት የነጋሪቱን ድምፅ ሰምታችኋል ? ከወደ ሳውዲ የተሰማው ያ የሲቃ ጩኸት፤ ያ ሮሮ፤ ያ እንምባ አስደንጋጩ የነጋሪት ድምፅ ነው። ከዚህ ድምፅ በኋላ ፋኖ ይሠማራል እንጂ አያለቅስም። ማልቀስ የናቁንና ያዋረዱን እንዲያከብሩን አያደርግም። ነጋሪቱ ከተጎሰመ በኋላ አገሬን፤ ክብሬን የሚል ተነስቶ ያያቶቹን ጋሻና ጦር ያነሳል እንጂ እንዲያው ዝም ብሎ አያጉረመርምም።አገር ተዋርዳ፤ ህዝብ ተበደሎ ዝም ብሎ ተንጋሎ የሚተኛ ካለ ይህን ብሄራዊ ውርደት ካመጡ ቡድኖች በምን እንደሚለይ ራሱን ይጠይቅ። አበቃን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!!**

---

### የሶማሌ ክልል የወያኔ ጦር መኮንኖች ገንዘብና ንብረት እንዲያካብቱ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ከፕሮጅቶች መካከል የቀብሪ ደሀር የውሀ አቅርቦት፣ የደገሀቡር የውሀ አቅርቦት፣ ጅጅጋ መምህራን ማሰልጠኛ ማስፋፊያ፣ የክልል የትምህርት ቢሮ ፕሮጀክት፣ ጅጅጋ አየር ማረፊያ አካባቢ የሚገኘው ዘመናዊ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ግንባታና ሌሎችንም ውድ ፕሮጀክቶች ይገኙበታል። ምንም እንኳ /ወ/ት ህዋ ግንባር ቀደም ሆነው ሀብቱን ቢቆጣጠሩትም ከጀርባ ሆነው የክልሉን ፕሮጀክቶች የሚያሰሩት ጄኔራል ዮሐንስ መሆናቸውን ምንጮች ይናገራሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ በክልሉ ውስጥ አሁን በመከላከያ አዛዥነት የሚንቀሳቀሱ አንድ የህወሀት የመከላከያ ኮሎኔል የክልሉ ፕሬዚዳንት የትውልድ ቦታ ላይ አንድ የውሀ ፕሮጀክት እንዲሰሩ የ120 ሚሊዮን ብር ተፈራርመው ስራውን ከጀመሩ በሁዋላና አስፈላጊው ክፍያ ከተፈጸመ በሁዋላ ፕሮጀክቱ አለመሳካቱን ምንጮች ገልጸዋል። ባለፈው ወር ለእኚሁ ኮሎኔል 22 ሚሊዮን ብር ከክልል መስተዳደር ወጪ ተደርጎ እንደተከፈላቸውም ምንጮች ገልጸዋል። ሰሞኑን በተከበረው የብሄር ብሄረሰቦች ቀን ዝግጅቶችን ከማዘጋጀት ጀምሮ የሽያጭ እቃዎችን እስከማቅርብ የሚደረሱ ስራዎችን ከህወሀት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በኮንትራት ወስደው ከፍተኛ ትርፍ እንዳገኙበት እነዚሁ የመስተዳድሩ የአስተዳደር ሰራተኞች ገልጸዋል።

................................................................................................................................................

## የወያኔ ዘረኝነትና ሙሰኝነት የአዲስ አበባን የመሬት ይዞታ ከተማዋ የማትወታዉ ማጥ ዉስጥ መክተቱ ተነገረ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እየተባባሰ የመጣዉን የመሬት ይዞታ ችግር ከሙሰኞቹ የወያኔ መሪዎች፤ ከቤተሰቦቻቸዉና ከጓደኞቻቸዉ በቀጥታ የተያያዘ ችግር ስለሆነ ልወጣዉ አልቻልኩም ሲል ማማሩን ዘጋቢዎቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። ከወያኔ ጋር ንኪኪ ያላቸዉ ግለሰቦችና የፓርቲ አባላት በአመለካከትም ሆነ በተግባር በሙስና ተዘፍቀው ተገኝተዋል ያለው የአስተዳደሩ ሰነድ፣ አዲስ አበባ ውስጥ ሕገወጥ የመሬት ወረራ፣ ሕገወጥ ግንባታና ሕገወጥ ንግድ አሁንም አሳሳቢ ችግሮች ሆነው ቀጥለዋል ብሏል፡፡ ከሰሞኑ የአዲስ አበባ ከተማ አመራሮችን ጠርቶ የመከረው አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቢሮ ችግሮች በስፋት የመልካም አሰተዳደር እጦት መገለጫ እየሆኑ መምጣታቸውን የቢሮው ሃላፊ አቶ ሰለሞን ሃይላይ ተናግረዋል፡፡የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቅርቡ በከፍተኛና በመካከለኛ አመራሮች ዙርያ ግምገማ አካሂዶ ትንታኔ የሰጠበት ሰነድ ማውጣቱ ይታወሳል፡፡

ከፍተኛ አመራሮች ሥራዎችን ጠበቅ አድርገው ከመሥራት ይልቅ ያዝ ለቀቅ እንደሚያደርጉ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ በሥራ የሚሰላቹና በተወሰኑ ሥራዎች የሚረኩ፣ የጠባቂነት ዝንባሌ የሚታይባቸው መኖራቸውን ጠቁሟል፡፡ በሌላ በኩልም የፀረ ሙስና ወይም ኪራይ ሰብሳቢ እና ሕገወጥነት ትግል በማካሄድ በኩል ዳተኝነት ይታያል፡፡ አልፎ አልፎም አንዳንድ አመራሮች በአመለካከትም ሆነ በተግባር የችግሩ ሰለባ ሆነው መገኘታቸውን ሰነዱ ያብራራል፡፡ ሰነዱ በመቀጠል አንዳንድ አመራሮች እነዚህን ችግሮች ታግለው ከማስተካከልና ሥርዓት ከማስያዝ ይልቅ አይቶ እንዳላየ ያልፋሉ፡፡ «በአጠቃላይ በአመራሮች መካከል የሚካሄደው የእርስ በእርስ ትግል ከአድርባይነት ያልፀዳ በመሆኑ ሊስተካከል ይገባል፤» ይላል ሰነዱ፡፡

አልፎ አልፎም በመርህ ላይ ተመሥርቶ ከመታገል ይልቅ በኔትወርክና በቡድንተኝነት መጠቃቃት በመካከለኛ አመራሮች አካባቢ ከሚታዩ ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ መሆናቸውን ሰነዱ ትንታኔ አቅርቦ አመራሮቹን ወቅሷል፡፡ በመካከለኛ አመራሩም ተመሳሳይ ችግሮች እንዳሉ ሰነዱ ትንታኔውን ያቀርባል፡፡ መካከለኛ አመራሮች የመሬት ወረራ፣ ሕገወጥ ግንባታና ሕገወጥ ንግድ በየአካባቢያቸው ሲስፋፉ አይተው እንዳላዩ የሚሆኑ አሉ ብሎአል፡፡ “አልፎ አልፎም በእነዚህ ጉዳዮች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ድርድር ያካሂዳሉ፣ ለሕገወጦች ሽፋን ይሰጣሉ፡፡ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ይደለላሉ የሚለው ሰነዱ፣ በተግባር ሙስና ውስጥ የተዘፈቁ መኖራቸውን ይዘረዝራል፡፡

እንደ ቢሮው ሃላፊ ገለፃ 40 ሄክታር መሬት፣ ሰዎች ከቦታው ሳይነሱ ፤ በምትኩም ሌላ ቦታ ሳይሰጣቸው በላያቸው ላይ ለኢንቨስትምንት ግንባታ ነፃ ያልሆነ መሬት ተላልፎ ተሰጥቷል፡፡ኅዳር 2004 ዓ.ም. የወጣው የሊዝ አዋጅ፣ መሬት በድርድር እንደማይሰጥ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን የከተማው አስተዳደር፣ ለአገር ይበጃል ያለው ፕሮጀክት፣ የሚፈልገውን መሬት ለካቢኔ አቅርቦ ማስወሰን እንደሚችል ጨምሮ ደንግጓል፡፡ ከዚህ ውጭ ለትልልቅ ፕሮጀክቶች በውስን ጨረታ እንዲሁም ለአልሚዎች በግልጽ ጨረታ ብቻ መሬት እንደሚቀርብ በአዋጅ መደንገጉ ይታወሳል፡፡ በአሁኑ ወቅት እየቀረቡ ካሉ ፕሮጀክቶች ውስጥ በውስን ጨረታ ሊስተናገዱ የሚችሉ ፕሮጀክቶች፣ አገራዊ ፋይዳ እንዳላቸው ተደርገው እንደሚታዩ የሚናገሩ አሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሊዝ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣው መመርያ የሐሳብ ልዩነት እንዳላቸው የሚገልጹ የአስተዳደሩ መሬት ሥሪት ባለሙያዎች፣ ሥራቸውን በተረጋጋ መንፈስ መሥራት እንዳላስቻላቸው ተናግረዋል፡፡

## የጋምቤላ ክልል ህዝብ በህንድና በሳዑዲ ኩባንያዎች ላይ ዕርምጃ እንዲወሰድ ጠየቀ

መሬቱ ተቀምቶ ለባዕዳን የተቸበቸበበት የጋምቤላ ህዝብ ወይ ከመሬቴ ወይ የመሬቱ ሽያጭ ያስገኛል ከተባለዉ የማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ጥቅም ተካፋይ መሆን አልቻልኩምና መሬቴን ይዘዉ አለስራ ዝም ብለዉ የተቀመጡት ባዕዳን ኩባንያዎች በአስቸኳይ የጋምቤላን ክልል ለቅቀዉ እንዲወጡ ጠየቀ። የጋምቤላ ህዝብ ይህንን ጥያቄ ያቀረበዉ ትላልቅ የመሬት ይዞታቸዎችን ተረክበዉ ምንም አይሰሩም ወይም ከፍተኛ ችግር ታይቶባቸዋል ደግሞም የፕሮጀክት አፈጻጸማቸዉ ደካማ ነው ያላቸዉን የተቀመጡት የህንድና የሳዑዲ አረቢያ ኩባንያዎችን ነዉ።የጋምቤላ ክልል መንግሥት በቅርቡ ለግብርና ሚኒስቴር፣ በግልባጭ ደግሞ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በጻፈው ደብዳቤ የህንድ ኩባንያዎች የሆኑትን ካሩቱሪንና ቬርደንታ ሃርቬስት፣ እንዲሁም የሼክ መሐመድ አል አሙዲ ኩባንያ የሆነው ሳዑዲ ስታር የእርምትና የማስተካከያ ዕርምጃ እንዲወሰድባቸው ጠይቋል፡፡

በጋምቤላ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ጋትሉዋክ ቱት ኮት ተፈርሞ የወጣው ደብዳቤ እንደሚያመለክተው፣ የክልሉ መንግሥት በነዋሪዎች አስተያየት ላይ ተመርኩዞ የራሱን ግምገማ አካሂዷል፡፡ ክልሉ ባካሄደው ግምገማ በተለይ እነዚህ ሦስት የውጭ አገር ኩባንያዎች ከፍተኛ ችግር እንደታየባቸውና የፕሮጀክት አፈጻጸማቸውም ደካማ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ከእነዚህ ኩባንያዎች መካከል ካሩቱሪ አግሮ ኢንዱስትሪ ተጠቃሽ ነው፡፡ ካሩቱሪ በ2000 ዓ.ም. በኑዌር ዞንና በኢታንግ ልዩ ወረዳ አንድ መቶ ሺሕ ሔክታር መሬት ወስዷል፡፡ ኩባንያው ከወሰደው መሬት ውስጥ 25 ሺሕ ሔክታር መሬት ላይ ምንጣሮ አካሂዷል፡፡ ነገር ግን ከመነጠረው መሬት ታርሶ በዘር የተሸፈነው ስምንት ሺሕ ሔክታር መሬት ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ በ7,750 ሔክታር በቆሎ፣ በ250 ሔክታር ሸንኮራ አገዳ አልምቷል፡፡ ነገር ግን ኩባንያው ሥራ ከጀመረ አምስት ዓመት ቢሆነውም እስካሁን ከሙከራ የዘለለ ለገበያ የቀረበ ምርት አለመኖሩ በክልሉ ተጠቅሷል፡፡

የክልሉ ፕሬዚዳንት ደብዳቤ እንደሚያስረዳው፣ ኩባንያው በቢዝነስ ፕላኑ ለአካባቢው ኅብረተሰብ ማኅበራዊ አገልግሎት የሚውሉ ግንባታዎችን እንደሚገነባ ቢገልጽም፣ ግንባታው ካለመካሄዱም በላይ የመሬት ግብርም በወቅቱ አልተከፈለም፡፡ኩባንያው የባሮ ወንዝ ወደ ማሳው እንዳይገባ በወንዙ ዳር የሠራቸው ግድቦች በአካባቢው ኅብረተሰብ ላይ ከፍተኛ ጎርፍ አደጋና ከፍተኛ የንብረትና እርሻ ውድመት አስከትለዋል ብሏል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው የህንዱ ኩባንያ ቬርዳንታ ሃርቬስት አግሮ ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ይህ ኩባንያ በ2000 ዓ.ም. በክልሉ ማጃንግ ዞን ጎደሬ ወረዳ 3,012 ሔክታር መሬት ተረክቧል፡፡ «ድርጅቱ ከመነሻው መሬቱን ሲረከብ ሻይ ቅጠል ለማልማት ቢሆንም፣ የእርሻ ሥራውን እያከናወነ የሚገኘው በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ ጥቅጥቅ ደንና ወንዞችና ጅረቶች በሚገኙበት ሥፍራ በመሆኑ፣ ብዙ ደን እየወደመና ወንዞችና ጅረቶችም እየደረቁ መሆናቸው እየተስተዋለ ነው፤» ሲል ክልሉ ለፌዴራል መንግሥት የጻፈው ደብዳቤ ያመለክታል፡፡

ክልሉ ለፌዴራል መንግሥት የጻፈው ይህ ደብዳቤ ያንፀባረቃቸው ሐሳቦች ከዚህ በፊት በነበሩት ጊዜያት የካዳቸው እንደነበሩ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ያስታውሳሉ፡፡ ይህ ኩባንያ የአካባቢው ነዋሪዎችና የአካባቢ ተቆርቋሪዎች እየሄደበት ያለው መንገድ አግባብ አለመሆኑን በተደጋጋሚ ሲገልጹ፣ የቀድሞው ፕሬዚዳንት አቶ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ታህሳስ 2003 ዓ.ም. ለግብርና ሚኒስትሩ አቶ ተፈራ ደርበው በጻፉት ደብዳቤ፣ «በምንም ምክንያት የደን መሬት ለእርሻ መሰጠት ስለሌለበት ደኑን ማልማት ለሚፈልጉ ሰዎች፣ ወይም በሕዝብ ተሳትፎ እንዲለማ ተገቢው እንዲፈጸም እጠይቃለሁ፤» ሲሉ ማሳሰባቸው ይታወሳል፡፡ ነገር ግን በወቅቱ የግብርና ሚኒስቴርም ሆነ የክልሉ መንግሥት ቦታው ቁጥቋጦ እንጂ የደን መሬት አለመሆኑ እየተጠቀሰ የቅሬታ አቅራቢዎች ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ይታወሳል፡፡ ከአራት ሳምንት በፊት የዚህ ኩባንያ ንብረት በእሳት የወደመ ሲሆን፣ በውድመቱ የተጠረጠሩ ስምንት ሰዎች በቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡

የክልሉ መንግሥት ይህንን እውነት ባመነበት ደብዳቤ ላይ ለኩባንያው የተሰጠው መሬት በደንና በወንዞች የተሞላ መሆኑን ከመግለጹም በላይ፣ ኅብረተሰቡ በቦታው ላይ የይገባኛል ጥያቄ እየቀረበና እሮሮም እያሰማ መሆኑን አምኖአል፡፡በሦስተኛ ደረጃ የተቀመጠው ሳዑዲ ስታር ግብርና ልማት ኩባንያ ነው፡፡ ይህ ኩባንያ በ2001 ዓ.ም. በአኙዋ ዞን አቦቦ ወረዳ አሥር ሺሕ ሔክታር መሬት ተረክቧል፡፡ ኩባንያው ሰባት ሺሕ ሔክታር መሬት ቢመነጥርም፣ አርሶ በዘር የሸፈነው 135 ሔክታር መሬት ብቻ ነው፡፡ ኩባንያው ወደ ሥራ ከገባ አምስት ዓመታት ቢያስቆጥርም በርካታ ሥራዎቹ በጅምር ቀርተዋል፡፡ ወደ እርሻ የሚወስደው ዋናው መንገድ በድርጅቱ ከባድ ተሽከርካሪዎች በየጊዜው እየተባላሸ ኅብረተሰቡ እጅግ የሚመረረበት እንደሆነና ይህንን መንገድ ሳዑዲ ስታር በአስፋልት ደረጃ ለመገንባት የገባውን ቃል እንዳላከበረ ክልሉ ለፌዴራል መንግሥት በጻፈው ደብዳቤ አስታውቋል፡፡ ሳዑዲ ስታር በከፍተኛ የማኔጅመንትና የፋይናንስ ቀውስ ውስጥ እንደሚገኝ መረጃዎች እየጠቆሙ ከመሆኑም በላይ የኩባንያው ንብረት ለጉዳት እንደተዳረገ ይነገራል፡፡

## ሰመጉ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ዉስጥ ወያኔ የዜጎችን . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በጥናቱ ወቅት ተፈናቃዮቹ ለሰመጉ እንዳስረዱት የደረሰባቸውን ከፍተኛ በደልና እንግልት በተለያዩ የሀገር ውስጥ ጋዜጦችና የውጭ ሚዲያ በመናገራቸው ምክንያት እስራት ዛቻና ክትትል እየተፈፀመባቸው እንደሆነና በከፍተኛ ስጋት ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል። ተፋናቃዮቹ ለረዥም አመታት ያፈሩትን ንብረትና የእርሻ መሬታቸውን በአካባቢው ባለስልጣናትና በሌሎች ብሔረሰብ አባላት መነጠቃቸውን፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶቻቸውን እንዳያዙበት መደረጋቸውን፣ መታወቂያ ካርድ እንዳያወጡ መከልከላቸውንና፣ ልጆቻቸው በትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብተው እንዳይማሩ መደረጉን ተናግረዉ “የዚህ ክልል ተወላጅ አይደላችሁም” እየተባሉ ዛቻ፣ ድብደባ፣ ንብረት ነጠቃና ለእሰራት ጭምር እንደተጋለጡ የተፈናቃይ ተወካዮች ለሰመጉ በፃፉት ማመልከቻ ተናግረዋል።

የባሩዳ ቀበሌ ተፈናቃዮች “ በአካባቢው አስተዳደር አካላትና በሌሎች የክልሉ ብሄረሰብ አባላት የተነጠቁትን የተለያዩ ንብረቶች ተመላሽ አለመደረጉን ፤በአሁኑ ወቅት ከሌሎች ብሄረሰቦች እየተለዩ ማስፈራሪያና ድብደባ እየተፈፀመባቸው መሆኑ፣ ምንም አይነት እገዛና ማቋቋሚያ አለመደረጉ፣ የእርሻ ግብዓትን እንደ ዘር ማዳበሪያ ያሉ ግብዓቶችን “እናንነተ የዚህ (ብሄር) አባላት ናችሁ” በማለት እየተከለከሉ ነገር ግን ለሌሎች እየተሰጠ እንደሚገኝና በፌዴራል መንግስት አማካኝነት ቢመለሱም የዞንና የቀበሌ አስተዳደር አካላት “እናንተ ከዚህ ክልል ውጪ ናችሁ” በማለት ልዩ ልዩ አድልዎና መገለል እየተፈፀመባቸው እንደሚገኝ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚገኙ የአማራ ተወላጆች ለረዥም አመታት ይኖሩበት ከነበረው ቦታ “ የዚህ አካባቢ ሰዎች አይደላችሁም” በማለት ከተፈናቀሉ በኋላ ወደ ነበሩበት ቦታ ይመለሱ እንጂ ምንም አይነት እገዛ ከመንግስት እንዳልተደረገላቸውና ይባስ ብሎም እንግልትና የተለያዩ አስተዳደራዊ በደሎች እየተፈፀመባቸው እንዳለ ዘጋቢያችን ሪፖርቱን ተከትሎ ባደረገው ማጣራት ለማረጋገጥ መቻሉን ገልጿል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

# ማን ነው የተዋረደው?

ይሄይስ አእምሮ ( ክፍል 3 የመጨረሻ ክፍል)

በመሠረቱና በእውነትም ብዙ ክፉ ነገሮችን ማድረግ በጣም ቀላል ነው። ዋናው ነገር ልክ እንደጥጋበኞቹ ዐረቦችና ተባባሪዎቻቸው ወያኔዎች ኅሊናን የመሳትና ወደአውሬነት የመለወጥ ጉዳይ ነው። በዚህ ሂደት ተዋራጁ ጨካኙ አውሬና ሰብኣዊነት በአጠቃላይ እንጂ የሚታረደውማ ዋናውን የዕልቂት በርኖስ ተከናንቦት እያለ የምን ውርደትን መደረብ ነው? እውነትን መነጋገር ከተፈለገ እንግዲያውስ የታረደ ከበረ። የታረደ በፈጣሪ ዘንድ የሰማዕትነትን ካባ ተጎናጸፈ። በከንቱ ጭዳ የሆነ የዘላለም ክብርን አገኘ። ተጠየቁ እንደዚህ ነው። የተዋረደው እዳር ቆሞ "አይዞህ ወንድሜ እረዳቸው፤ ቀብጠዋልና ጉልበትህን አሳያቸው፤ እኛን ጠልተው ከሀገር ስለወጡ ቀኝ እጃችንን አውሰንሃልና እንደፈለግህ አድርጋቸው" እያለ በስቃይ የሚደሰት ወገን ነው። ጊዜው ሲደርስ ወዮ ለዚህ ዓይነቱ ፍጡር! እናም ውድ ኢትዮጵያውያን ለቅስቀሳ ፍጆታው ያህል ልክ ነው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ተዋርደናል፤ ተንቀናል፤ ከዚያም በላይ። እንደእውነቱ ከሆነ ግን የተዋረደው ዓለም ነው፤ የተናቀው የሰው ልጅ ዘር በአጠቃላይ ነው፤ የታረደው በትዕቢትና በዕብሪት አንገታችንን እየቆለመመ በሠይፍና በጎራዴ እየቀነጠሰን ያለው በሌላኛ ጠርዝ የሚገኘው የሰይጣን አሽከርና ሎሌ የሆነው የሰው ልጅ ነው። እንጂ ኢትዮጵያማ በአሁኑ ሰዓት በጽርሓ አርያም ከሁሉም በበለጠ ክብርና ሞገስ እየተሸሞነሞነች ናት። የዚህን አያዎኣዊ(paradoxical) አነጋገር አንድምታዊ ፍቺ ወደፊት ምናልባትም በቅርብ የምናየው ይሆናል። … የተዋረድን የመሰልነው ደግሞ በውጭ ብቻ እንዳልሆነ እናውቃለን። ወያኔ እስካለ ክብር የለንም፤ ከነአካቴውም እንደሰው አንቆጠርም። የሁሉም መጫወቻ ነን።

እንደብዙዎች ዜጎች ኢቲቪን አልመለከትም። ስመለከት በሽታየን የሚቀሰቅስ አንዳች ነገር ስለማገኝ አላይም - ስህተት ነው - ግን ምን ላድርግ፤ ከጤና የሚበልጥ ነገር ደግሞ የለም። ዛሬ ለምሳሌ ትልቅ በሽታ ነው የተቀሰቀሰብኝ። ወደሌላ ጣቢያ ላልፍ ስል ድንገት ኢቲቪን ስከፍት ኃይለማርያም ደሳለኝ የሚባለው ዳግማዊው መቶ አለቃ ግርማ ወ/ጊዮርስ በወቅቱ የወገኖቻችን አሰቃቂ ጉዳይ በ"ጋዜጠኛ" እየተጠየቀ አየሁ፤ ኃይለማርያም ደንቆሮና በልጆች ቋንቋ ጀዝባ መሆኑን ዛሬ ከእስከዛሬው በበለጠ ልብ አልኩ። ራሴን እንደምንም አሳምኜ ትንሽ ልከታተል ወሰንኩና ማየቴን ቀጠልኩ። ግን የጋዜጠኛ ተብዬውና የሰውዬው የአቀማመጥ ሁኔታ ራሱ ትልቅ የፕሮቶኮል ችግር ስላለበት መከታተል አትበሉት - እየቀፈፈኝ እንደምንም ለጥቂት ደቂቃዎች ታገስኩና ተከታተልኩ።

ጋዜጠኛው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ተብዬው ደግሞ ጋዜጠኛ መስለዋል። ጋዜጠኛው እግሮቹን አጣምሮ ተንቀባርሮና እጅግ ተዝናንቶ ‹ሲጠይቅ›፣ ኃ/ማርያም እግሮቹን በሥርዓቱ ዘርግቶ ሽቁጥቁጥ እያለ ሲመልስ አንጀትን ይበላል - በ"ሥርዓቱ" ባልኩበት መንገድ መቀመጡ ጥሩ ሆኖ የ"ጋዜጠኛው" "ጠቅላይ ሚኒስትራችን"ን በማንጓጠጥ መልክ እግሮቹን አጣምሮ መጠየቁ ነው የቆጨኝ - በጠቅላይ አሽከሩ አማካይነት የናቁን ግብጾችና ሳዑዲዎች ብቻ ሣይሆኑ ጋዜጠኞቻችንም ናቸው ማለት ችያለሁ፤ ወያ በሚያገኘው አጋጣሚ ሁሉ ኢትዮጵያን ለማዋረድ የማይፈነቅለው ድንጋይ አለመኖሩን ስረዳ የወያኔን ሥነ ልቦናዊ ደዌ የክብደት ደረጃና የኛን የምሕረት ዘመን መንቀራፈፍ አስታውሳለሁ። ይህ ነገር መለስን እንዳንረሳ ሲባል በወያኔዎች ሆን ተብሎ የተቀናበረም ይመስላል። የሚናገረውን ብቻም ሣይሆን እንዴት መቀመጥ እንዳለበትም መመሪያ ቢጤ ሳይሰጡት አልቀረም። ቤተሰቤ በሙሉ ነው በዚህ ነገር የተሸማቀቀው። በርግጥም አቶ መለስን አስታወስነው - ተሳክቶላቸዋል። አቶ መለስ ‹ጋዜጠኞቹን› እንዴት እንደሚገላምጣቸውና አጥንተው ከመጡት ይጠይቁትን ያሳጣቸው እንደነበር ትዝ አለኝ። ከመሞቱ አጎደለን ማት ነው? በርግጥም እኮ መለስ ቢኖር ኖሮ ሳዑዲዎችም ይህን ያህል አይማግጡም ነበር ብሎ መገመት ይቻላል። በርግጥም እኮ መለስ ቢኖር ኖሮ ግብፆች በኃ/ ማርያም ላይ እንዳፌዙበት በርሱ ላይ አያፌዙበትም ነበር። ስለዚህ ወያኔ የቀረው ጊዜ አንድ ወርም ይሁን አንድ ዓመት ለምን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንዱ ወያኔ አይሆንልንም? እውነቴን ነው - እንደለመድነው አንዱ ትግሬ ቁጭ ይበልበትና ይህን ኮንዶም ሰውዬ ወደማስተማር ሙያው ይመልሱት። "ውርደታችን" እኮ ለከት አጣ። በንነው እስኪጠፉ ድረስ በዚህች እንኳን አንዋረድ። በአሁኑ ሰዓት እኮ ኢትዮጵያውያንን እንደውዳቂ ዕቃ የማይቆጥርና እንደጠፍ አህያ ልቡ እስኪጠፉ የማይጭን የለም። እስኪያልፍ ያለፉልና አይዞን!!!

በቅድሚያ ይህ ሰውዬ ብዙዎች እንደሚሉትና በብዙዎች እንደሚታመነው ከአንድ ሀብታም ሰው የቤት ጠባቂ ያነሰ የስብዕና ደረጃና የሥራ አፈጻጸም ሥልጣን ያለው መሆኑ ፀሐይ የሞቀው ነገር ነው። የዚህ ሰውዬ ጭንቅላት ሥሪት ምን እንደሆነ ግራ የሚያጋባ በመሆኑ እንጂ እኔ እሱን ብሆን እንደዚህ መሣቂያና መሣለቂያ ሆኜ መኖርን አልመርጥም ነበር - የሰው ተፈጥሮ ግን በውነቱ አስገራሚ ነው። ከኃይለማርያም ደሳለኝ ይልቁንስ የፍቅር እስከመቃብሩ ፊረጃ ይሻላል፤ "ፊረጃ በሚለው የባሪያ ስሜ የሚያውቀኝ ሰው ምን ይለኛል?" በሚል መዘባበቻ ያደርገኛል ብሎ የፊራውን ዕዝራ የሚለውን አዲሱን ስሙን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነም - ባህሉንና ማኅበረሰብኣዊ አወቃቀሩን ተረድቶታልና የሰው የሃሜት ግርፋት አስቀድሞ የታዬው ይመስላል። (ይህን ስል ነገሮችን ለንጽጽር አስቀመጥኩ እንጂ ፍርድ ውስጥ እንዳልገባሁ ማስታወስ እፈልጋለሁ)። በዚህ መልክ እየተሸቆጠቆጠ አንድም የራሱ ቃል ሳይኖረው (with out any say in 'his' government) የሰጡትን የሚያስተላልፍ አሽንዳ ሆኖ መኖሩ ምን ዓይነት እርካታና ደስታ እንደሚያገኝበት አይገባኝም። አለኝ ከሚለው ሃይማኖትም ሆነ ከራሱ ኅሊና ጋር እንደተጣላ እስከመቼ በሌሎች ሰዎች ጭንቅላት እየተመራ - ለቃሉ አጠራር ይቅርታ ይደረግልኝና - ኮንዶም ሆኖ እንደሚኖር አላውቅም። ራሱ ነጻ ቢወጣ ይሻለዋል። ኃይለማርያም ራሱን ቢሆንና በነጻይቱ ኢትዮጵያ ባሰኘው የሥልጣን እርከን ተወዳድሮ በራሱ አእምሮ የሚንቀሳቀስበትን መድረክ ቢጠብቅ፣ ለዚሁ መድረክ እውንነትም የበኩሉን ትግል ቢያደርግ እንደሚሻለው በዚህ አጋጣሚ ብጠቁም ብዙ የዘገየሁ አይመስለኝም። ካሰበበት ይችላል። አሁን ካለበት የጥፋት መንገድ ግን በአፋጣኝ ይውጣ። ክፉኛ መሽቷል። ወያኔ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የሚዳክር፣ በራሱ ኃይልና ጥበብ ሳይሆን በአጋጣሚዎች መወሳሰብ ብቻ እስትንፋሱ ብን ብን እያለች የሚኖር ድርጅት ነው። እንደሚመስለኝ ወያኔ እንዳይወድቅ እያገዘው ያለው የጥቂቶች ብፁዓን አባቶች ጸሎት ነው፤ መውደቁን የምንመኘው ዜጎች ራሳችንን ሳናስተካክል እንዲሁ በባዶ ሜዳ ርስ በርስ እየተናቆርን በምንገኝበት ሁኔታ ወያኔ አሁን ቢወድቅ ጦሱ ብዙ፣ መዘዙም በቀላሉ የማይወገድ ነው። በመቶዎች የተከፋፈለ ፖለቲከኛ፣ ለሥልጣን የቋመጠ ጎጠኛ፣ በዘር የተቧደነ ጦረኛ፣ ለበቀል ያሰፈሰፈ ሽፍጠኛ፣ ለሀብት የተስገበገበ ሆዳም፣ … በየጉራንጉሩ አንዳች ዕድል በሚጠባበቅበት ሁኔታ ይህ በቁሙ ሞቱን ጨርሶ ጣር ላይ ያለ የማፊያ ቡድን ለይቶለት እንዳይወድቅ እኔም ብጸልይ የሚኮንነኝ እንዳይኖር እማጠናለሁ። መውደቅ ያለበትን ጊዜ በበኩሌ አውቃለሁ። ያም ቀን አሁንና ዛሬም ሊሆን በቻለ። ግን ፈጣሪ የታከለበትና ሌላ አደጋ የማያስከትል እንዲሆን የምንመኝ ብቻ ሣይሆን በርትተን የምንጸልይ ወገኖች አንጠፋምና ጌታ ይሰማናል። ችግሩ የመንግሥት ለውጥ አይደለም። መንግሥት መቼም ሊለወጥ ይችላል። ዋናው ነገር ‹አሮጌው ወይን በአዲሱ አቅማዳ እንዳይገባ› የመጠንቀቅ ጉዳይ ነው - ለኢትዮጵያ ደግሞ ከሰው በላይ የሚጠነቀቅላትና የሚጨነቅላት አምላክ አላት፤ እንደሰው ቢሆንማ እስካሁን ድረስም ቢያንስ በሕይወት መቆት ባልተቻለን ነበር - ወርቁ ጠፍቶ ሚዛኑ ያለው በአንድዬ ተራዳኢነት ብቻ ነው - ይህን አንተ ላታምን ብትችል አልፈርድብህም - ምክንያቱም የሰቆቃው ዘመን በእጅጉ በመራዘሙ ሳቢያ ከአምላካችን ጋር የተጣላን ዜጎች ቁጥር ብዙ መሆኑን መገንዘብ አያስቸግርምና። እንጂ በመሪና በመንግሥት መለወጥማ መንግሥቱስ በመለስ ተተክቶ አልነበረምን? እናም በዚህ አምናለሁ - ወያኔን መጣል የሴከንዶች ጉዳይ ነው። እንዲያውም ሴከንዶችንም ላይፈጅ ይችላል። ዱሮውን የወደቀ ነውና - የታመመ ሰው ሲሞት እኮ ሳይተጣጠብ፣ ሳይከፈንና ሳይበጃጅ መሞቱ ለቤተሰብ ተነግሮ እንዲለቀስ አይደረግም፤ የወያኔም ነገር እንደዚሁ ነው - ከሞተ ቢቆይም ገናዥ እስኪገኝ - ገናዦች እስኪስማሙና ወደሬሣ ክፍል ደፍረው እስኪገቡ ድረስ ኅልፈቱ አይነገርም፤ "እባብ ልቡን ዐይቶ እግሩን ነሣው" - ወያኔም እንደ እባብ አናቱን ተቀጥቅጦ እንደድመት በዘጠኝ ነፍስ፣ ከዘጠኙም በመጨረሻዋ ይኖራል - "የተበዮች አለመስማማት ለበዮች ይመቻል"። አሁን የሚታየው ትልቁ ነገር ወያኔን ሥልጣን የሚረከበው አጥቶ ራሱንም በሚገርመው አኳኋን ሀገሪቱ ሰው አልባ ሆና መቅረቷ ነው - ይህ ካልሆነ በስተቀር ወያኔ አልሞተም ተብሎ ሊዋሽ የሚችልበት አንድም ሀገራዊ ሁኔታ የለም። ይህም ሥራ የተሠራው በደርግ፣ በወያኔ በራሱና የኢትዮጵያን ኅልውና በማይፈልጉ የውጭ ኃይሎች ነው - ኢትዮጵያ ከአናት ተመታች - ለጊዜው እስትንፋሷ ፀጥ አለና የሞተች መሰለች፤ "hibernate" ባደረገው ሕይወት ያለው በድኗም ላይ ወያኔ እንደልቡ ተንጎማለለባት - የማይቀር ፍርድ ነበረና እንደምንም ተወጣነውና ይህም ክፉ ቀን ሊያልፍ የምሥራቹ ደረሰ። ፈጣሪ እሾህ አሜከላውን ሲገፍላት፣ ይህን የ80 ሚሊዮኖች የአስተዳደር ወንበር ሊረከቡ የሚችሉ የበቁ ዜጎች ፈጣሪ ፈልጎ ሲያገኝና ከያሉበት ሲያሰባስብ ኢትዮጵያ ምን በመሰለ ክብርና ሞገስ እንደምትነሣ ለማየት ያብቃን። እንዲህ በል አለኝ እንዲህ አልኩ። በትንሣኤዋ የሚፈራ ይፍራና ይውጣለት። የማይቀርን መናገር ነውር አይደለም። ሞቶ መነሳት በግለሰብ እንጂ በሀገር ደረጃ በጣም ቀላል ነው። ሞቶ ያልተነሳ ሀገር የለም።

ኃ/ማርያም ከተናገረው ፍሬፈርስኪ አንዱ አስገርሞኛል። በዚህ በወቅቱ የዜጎቻችን በ‹ቅጡ አለመያዝ› ምክንያት ስለሳዑዲና ኢትዮጵያ ወዳጅነት መጠልሸት መቻል አለመቻል ሲጠየቅ "በዚች ክስተት፣ በዚህች ትንሽ ነገር" በማለት ይህን በሙሉጌታ ሉሌ አነጋገር - ቃል በቃልም ባይሆን ጭብጡን ልጥቀሰው - "ይህ ሳዑዲ ዐረቢያ ውስጥ በሀገራችን ዜጎች ላይ የተከሰተው ዕልቂትና ስቃይ መንግሥት ቢኖረን ኖሮ ጦርነት የሚያሳውጅ ታላቅ ሀገራዊ ጉዳይ ነው፤ ብዙ የዓለም ጦርነቶች የተቀሰቀሱት ከዚህ በሚያንሱ ትናንሽ አጋጣሚዎች ነው። ይህ የኛው ጉዳይማ ወዲያውኑ ከተት የሚያስብል ነው።…" ተብሎ የተመሰከረለትን ሀገራዊ ታላቅ ጉዳይ እንደተራ የጎረቤት ጠብ ቆጥሮት ዐረፈው። ያኔ የዚህን ሰውዬ ኢትዮጵያዊነት ብቻ ሳይሆን አእምሮኣዊ ጤንነቱንም ተጠራጠርኩ። አቶ መለስ እንደዚህ ያሉ ጀዝባ ሆዳሞችን፣ እንደደመቀ ያሉ ደናቁርት ጌኞዎችን መርጦ አጠገቡ ማስቀመጡ ለወያኔው ሥርዓት ዕድሜ መራዘም በርግጥም ጠቅሞታል። እናላችሁ ይህን ላንቃችን እስኪበጠስ እያስጮኸን የሚገኘውን ታላቅ ጉዳይ፣ ደም እስክናነባ እያስለቀሰን የሚገኘውን የሚሌንየም ሰቆቃ እንደቀላል ነገር ቆጥሮ "በዚች ክስተት ወዳጅነታችን አይሻከርም…" ብሎን ዕርፍ። ይህ - በነሱው ቃል - ወደር የማይገኝለት ተንበርካኪነት ወያኔዎች ከሕዝብ ስለተጣሉ ከዐረቦቹም ጋር ላለመቀያየምና በል ልዩ ሰበብ አስባቦች ከነዳጁ ዶላር ለመመጽወት ካላቸው ጽኑ ፍላጎት የሚመነጭ እንጂ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ቢኖረን ኖሮ ሰው አይደለም አንዲት ጥንቸልም ብትገደልብን ብሔራዊ ጦርነት ያሳውጃል። አንደኛውን ይሁን ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት የቀሰቀሰችው እኮ አንዲት ዓሣማ ናት አሉ። እንዲያው ለነገሩ ግን በወገን ደም ለመቀለድ ይህን ያህል ድንቁርናና የገረረ ቆዳ ከየት አመጡት? በዘርና በቋንቋ ተመሥርተው በስቃይ ላይ ከሚገኙ ወገኖች የራሴ ናቸው የሚሏቸውን ዜጎች እየመረጡ ወደ ሀገር መመለስንስ እንዴትና ከየትስ ተማሩት? የበረሃው ወያኔ ከ23 ዓመታት በኋላ እንዴት ይህን ዓይነቱን የጫካ የመድሎ አሠራር አይረሳም? ቂም በቀልንና የነገር ቁርሾን ለአፍታም እንዳይዘነጉ ምን ዓይነት ሶፍትዌር ይሆን በየጭንቅላታቸው ያስገጠሙት? ለነሱም ሆነ ለኛ ምን ዓይነት መረገም ይሆን? የሚመለሱትን ብዙዎቹን ስትመለከቱ እኮ የሕወሓት የጦር ባታሊዮን ይመስል ቋንቋቸው … ምንም ይሁን … ያው ግን ወገኖቻችን ናቸውና ምን ይደረጋል፤ ሀዘናችንና ልቅሶኣችን ቅጥ አጣ - ሚቱም ገዳዩም እቤቷ መሸገውባት አትስቀው አታለቅሰው ነገር ሆነባትና ግራ ገብቷት እንደተቸገረችው ያቺ ምሥኪን ወይዘሮ ሆነናል። ብቻ ግን ከዚህ ሁሉ የመንግሥትነት ዘመን በኋላ እንደዚህ ያለ አድልዖ ሲታይ ክፉኛ ያምማል። በዚህ የግሎባላይዜሽን ዘመን የሰው ዘር ስለሰው ዘር መጨነቅ ሲገባው ሊያውም የሁላችን የምንለው መንግሥት የኤምባሲዎቻችንን ሥራና ባጀት ለራሱ ሰዎች ብቻ ማዋሉ ከማሳዘን ያለፈ የሀገር ሸክምና ዕዳ ነው። ሌላው ኢትዮጵያዊ በዐረቦች እንዲጨፈጨፍ ተትቶ የራስ የሚሉትንና መዋጮና ድጋፍ ያደርግ የነበረን እየመረጡ ከእሥር ማስፈታት፣ ቅድሚያም ሰጥቶ ወደሀገር ማስገባት … ነገ የሚያመጣውን የዞረ ድምር ካለማየት የሚመጣ ድንቁርና ነው። አቤት የዚህ ዘመን ትንግርት! እግዚአብሔር ሆይ ቶሎ ናልን!!

yiheyisaemro@gmail.com